የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሣኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 52
ADDIS ABABA 1st August, 2024

**<u>ማውጫ</u>**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴፱/፪ሺ፲፮

የኢሚግሬሽን (ማሻሻያ) አዋጅ ……..ገጽ ፲፭ሺ፯፻፷፮

**<u>Content</u>**

Proclamation No. 1339/2024

Immigration (Amended) Proclamation ………..
……………..………..........................Page 15766

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴፱/፪ሺ፲፮

## <u>የኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፬/፩ሺ፱፻፺፭ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>

አዋጁ ከወጣ ረዘም ያለ ጊዜ ያሳለፈና የዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ ሁኔታዎችን ለውጥ ተከትሎ የሚመጡ ለውጦችን ለማስተናገድ የሚያስችል አሰራር ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤

ከሌሎች ሀገራት ጋር የተጣጣመ የጉዞ መረጃና ምዝገባ ሥርዓት እንዲኖረን እና በሀገሪቱ መውጫና መግቢያ በሮች የሚተላለፉ ሰዎች ሕጋዊነትን በማረጋገጥ ወንጀልን በቀላሉ ለመከላከል እና በሀገር ላይ ሊደርስ የሚችልን ማህበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ለመቀነስ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀፅ ፶፭(፪)(ሠ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢሚግሬሽን (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴፱/፪ሺ፲፮ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1339/2024

## <u>A PROCLAMATION TO AMEND THE IMMIGRATION PROCLAMATION NO. 354/2003</u>

**WHEREAS,** it has become necessary to put in place a procedure to accommodate the changes that have passed since the proclamation was issued and the changes that follow the changes in international and national conditions;

**WHEREAS,** it has become necessary to have a travel information and registration system in line with other countries and to ensure the legitimacy of people passing through the country's exit and entrance gates, it is necessary to amend the proclamation to easily prevent crime and reduce the social and economic damage that may be caused to the country;

**NOW, THEREFORE,** by Article 55(2)(e) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

### 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Immigration (Amended) Proclamation No. 1339 /2024" ".

## ፪. ማሻሻያ

የኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፬/፩ሺ፱፻፺፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተተክቷል፡-

“፪/ “አገልግሎት” ማለት የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ነው፡፡

፪/ ከአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፭) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች (፮)፣ (፯)፣ እና (፰) ተጨምረዋል፡-

፮/ “አጓጓዥ” ማለት አግባብነት ባለዉ ሕግ መሠረት መንገደኛን ወደ ኢትዮጵያ ይዞ የሚገባ ወይም የሚወጣ ሰው ነው፤

፯/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፰/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

፫/ በአዋጁ በማናቸውም ስፍራ “ባለስልጣኑ” ተብሎ የተጠቀሰው “አገልግሎቱ” ተብሎ ይነበባል፡፡

፬/ የአዋጁ አንቀፅ ፫ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተተክቷል፡-

“፪/ የቱሪስት፤ የትራንዚት፤ ለአጭር ስብሰባ፣ ወርክ ሾፕ ወይም አውደ ጥናት፤ የሚዲያ ሥራ፤ ሃይማኖታዊ፤ ወይም የስፖርት ቪዛ ያለው የውጭ አገር ዜጋ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተዘረዘሩት በተጨማሪ፡-

ሀ) መመለሻ ወይም ወደ ሌላ አገር ለመጓዝ የሚያስችል የጉዞ ትኬት፤ እና

ለ) እንደአስፈላጊነቱ ሊሄድ ወደ አሰበው ሀገር የሚያስገባ የፀና የመግቢያ ቪዛና የጤና ማስረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡”

፭/ የአዋጁ አንቀፅ ፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፯ ተተክቷል፡-

## 2. Amendment

Immigration Proclamation No. 354/2003 is here by amended as follows:

1/ Sub-Article (2) of Article 2 of the Proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Sub-Article (2):

“2/ “Service” means the Immigration and Citizenship Service.

2/ the following new Sub-Article (6), (7) and (8) are added next to the Sub-Article (5) of Article 2 of the Proclamation:

6/ "Carrier" means a person who carries a passenger to Ethiopia by the law who comes in or out;

7/ "Person" means any natural or judicial person;

8/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

3/ Referred to as "the Authority" in any place of the Proclamation shall be read as "the Service".

4/ Sub-Article (2) of Article 3 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2):

"2/ In addition to those listed under Sub-Article (1) of this Article a foreign citizen who has tourist, transit, short meeting, workshop; media work; a religious or sports visa shall possess:

a) a travel ticket for return or travel to another country; and

b) a valid entry visa and health certificate shall have to enter the country he intends to travel to as deemed necessary."

5/ Article 7 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 7:

"፯. **ከኢትዮጵያ እንዳይወጡ ስለሚታገዱ ሰዎች**

፩/ ማንኛውም ሰው ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ ሊታገድ የሚችለው በሕግ መሠረት በፍርድ ቤት ሲታዘዝ ነው፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ቢኖርም የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር ከሚመለከታቸዉ የደህንነት አገልግሎት እና ሕግ አስከባሪ አካላት ከሚያገኘዉ መረጃ ወይም አገልግሎቱ በራሱ ከሚያገኘዉ መረጃ በመነሳት በብሔራዊ ጥቅም እና ደህንነት ላይ ሊቀለበስ የማይችል ግልፅና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ሁኔታ መኖሩን ሲያምን ማንኛውንም ሰው ከአገር እንዳይወጣ ማገድ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ከሀገር እንዳይወጣ የታገደ ሰው ስልጣን ያለው ፍ/ቤት እግዱን ካላፀናው በስተቀር ከ፫ (ሶስት) የሥራ ቀናት በኋላ እግዱ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፮/ ከአዋጁ አንቀፅ ፲፫ ንዑስ አንቀፅ (፩) ፊደል ተራ (መ) ቀጥሎ አዲስ ፊደል ተራ (ሠ) ተጨምሯል፡-

"ሠ) በሃይማኖታዊ ወይም በህክምና ቪዛ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የውጭ ሀገር ዜጎች ከገቡበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ፡፡

፯/ ከአዋጁ አንቀፅ ፲፮ ንዑስ አንቀፅ (፪) ፊደል ተራ (ለ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሐ) ተጨምሮ ነባሩ ፊደል ተራ (ሐ) ፊደል ተራ (መ) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡-

"ሐ) በአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር እውቅና በአገሪቱ በሚገኙ የውጭ አገር ሰዎች ላይ በመንግሥት የሥራ ሰዓትና ቀን ድንገተኛ የመስክ ቁጥጥር ያደርጋል፤"

፰/ የአዋጁ አንቀፅ ፲፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፲፯ ተተክቷል፡፡

"7. **People Who Will be Banned from Leaving Ethiopia**

1/ Any person shall be banned from leaving Ethiopia if ordered by the court by law.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the Director General of the Service may suspend any person from leaving the country based on information obtained from relevant security service and law enforcement organs or the information obtained by the Service itself and he believes that there is a clear and substantial harm that cannot be reversed in the national interest and security.

3/ According to Sub-Article (2) of this Article, the ban will not be enforced after 3 (three) working days unless the competent court maintain the ban.

6/ A new paragraph (e) is added next to the letter (d) of Article 13(1), of the Proclamation:

"(e) Foreign persons entering Ethiopia on a religious or medical visa within 30 days from the date of entry.

7/ "the following new paragraph (c) is added next to the paragraph (b) of Sub-Article (2) of Article 16 of this Proclamation, the existing paragraph (c) renumbered as paragraph (d):

"c) By the recognition of the Director General of the Service on foreign persons in the country shall provide emergency field control during government working days and hours;"

8/ Article 17, of the Proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Article 17.

"፲፯. **<u>የአጓጓዥ ኃላፊነት</u>**

፩/ ማንኛውም አጓጓዥ መንገደኛን ወደ ሀገር ለማስገባት ወይም ከሀገር ለማስወጣት ከማጓጓዙ ከሶስት ሰዓት በፊት የመንገደኛውን ቅድመ ጉዞ መረጃ እና ስም ዝርዝር ለአገልግሎቱ ማሳወቅ ወይም መላክ አለበት፡፡

፪/ የውጭ አገር ሰው ወደ ኢትዮጵያ ይዞ የሚመጣ አጓጓዥ መንገደኛው በአዋጁ አንቀፅ ፫ የተመለከተውን የፈፀመ መሆኑንና በአዋጁ መሠረት በሚወጣ ደንብ በተወሰነው መግቢያ በር መውረዱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ ከኢትዮጵያ የሚወጡ መንገደኞችን ያሳፈረ ማንኛውም የአየር ትራንስፖርት አጓጓዥ የመንገደኞቹን ቅድመ ጉዞ መረጃ እና ስም ዝርዝር ከማጓጓዙ ከሶስት ሰዓት በፊት ወደሚሄድበት አገር ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም ከአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ውጭ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ አጓጓዥ በስምምነት ወይም በእንካ ለእንካ መርህ መሠረት የመንገደኞችን ቅድመ ጉዞ መረጃ እና ስም ዝርዝር ወደሚሄድበት አገር ከመድረሱ በፊት ማሳወቅ አለበት፡፡

፭/ በአዋጁ አንቀፅ ፳፩ (እንደተሸጋሸገ) ንዑስ አንቀፅ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና ንዑስ አንቀፅ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣(፪) እና በአዋጁ አንቀፅ (፫) የተመለከተውን የተላለፈ አጓጓዥ ያመጣውን መንገደኛ በራሱ ወጪ መመለስ አለበት፡፡"

፱/ ከአዋጁ አንቀፅ ፲፰ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፲፱ ተጨምሮ ነባሮቹ ከአንቀፅ ፲፱ እስከ ፳፬ የነበሩት ከአንቀፅ ፳ እስከ ፳፭ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

"17. **<u>Obligations of Carriers</u>**

1/ Any carrier shall notify or send the service the advanced passenger's information and name list three hours prior to the departure of a passenger for entry or deportation.

2/ A carrier carrying a foreign person to Ethiopia must ensure that the passenger has fulfilled the provisions of Article 3 of the Proclamation and has disembarked at the gateway determined by the Regulations issued by the Proclamation.

3/ Any air transport carrier that embarks passengers departing Ethiopia shall notify the advanced passengers' information and name records to the country to which he is going three hours before departure.

4/ Any carrier providing transportation services other than air transport services shall disclose the advanced passenger's information and names of passengers before arriving in the country to which they are traveling, by the agreement or principle of give and take.

5/ Without prejudice to paragraph (a) of Sub-Article (1) and Sub-Article (2) of Article 21(as re-arranged) of this Proclamation, the carrier violets provision of Sub-Articles (1) , (2) of this Article and Article (3) of this proclamation shall return the person transferred at its own expense."

9/ The following new Article 19 is added Next to Article 18 of the Proclamation and the existing Articles 19-24 are re-arranged as 20-25:

"፲፱. **<u>የውጭ አገር ሰው የሚያሰራ ሰው ኃላፊነት</u>**

፩/ ማንኛውም የውጭ አገር ሰው ለሥራ ወይም ለተለያየ አገልግሎት ወደ አገር ማስገባት የሚፈልግ ሰው አስፈላጊ መረጃዎችን አሟልቶ ለአገልግሎቱ ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለበት ሰው ግንኙነቱ ካስመዘገበው ሰው ጋር ሲቋረጥ ለአገልግሎቱ በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የሕግ ሰውነት ያለው ሰው የሚፈልገውን አገልግሎት በተወካይ ለማግኘት ይህንኑ የሚያስፈፅም ተወካይን ለአገልግሎቱ ማስመዝገብ፤ የተወካይ ለውጥ ሲኖርም ለአገልግሎቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ የዚህ አንቀፅ ዝርዝር አፈፃፀም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡"

፲/ ከአዋጁ አንቀፅ ፳ (በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ እንደተሸጋሸገ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፳፩ ሆኖ የተጨመረ ሲሆን ነባሮቹ ከአንቀፅ ፳፩ እስከ ፳፭ (በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 እንደተሸጋሸገ) የነበሩት አንቀፆች ፳፪፣ ፳፫፣ ፳፬፣ ፳፭፣ እና ፳፮ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

"፳፩. **<u>አስተዳደራዊ ቅጣት</u>**

ማንኛውም ይህን አዋጅ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ ወይም መመሪያን የጣሰ ሰው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡"

፲፩/ የአዋጁ አንቀፅ ፳፫ (እንደተሸጋሸገ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፳፫ ተተክቷል፡-

"19. **<u>Responsibility of a Person Working with a Foreigner</u>**

1/ Any person who wants to bring in a foreign person to the country for work or other services must complete the necessary information and register for the Service.

2/ The person who is obliged to register under Sub-Article (1), of this Article shall notify the Service within three working days of the termination of the relationship with the registered person.

3/ Any legal person shall register a representative for the Service in order to obtain the services required by a representative, and in the event of a change of representative, he shall notify the Service.

4/ The detailed implementation of this Article shall be determined by the Directives to be issued for the implementation of this Proclamation."

10/ the following new Article is added as Article 21 Next to the Article 20, of this Proclamation (as re-arranged by Article 7 of this Proclamation) and the existing Articles 21 to 25 (as re-arranged by Article 7 of this Proclamation) are hereby re-arranged to be Articles 22, 23, 24, 25 and 26:

**"21. <u>Administrative Penalty</u>**

Any person who violates this Proclamation, any Regulation or Directive issued under this Proclamation shall be subject to administrative measures by the Regulations issued by the Council of Ministers."

11/ Article 23 of the Proclamation (as re-arranged), is hereby deleted and replaced by the following new Article 23:

"፳፫. **ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ አገልግሎቱ ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡"

፫. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

"23. **Power to Issue Directives and Regulations**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Service may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued under this Proclamation.

3. **Effective Date**

This Proclamation shall be effective starting from the date of its approval by the House of People's Representatives.

**Done at Addis Ababa, on this 1st Day of August, 2024**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**